አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Second year No. 31
ADDIS ABABA 18th day of March, 2010

ማውጫ

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎችን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ......................ገጽ** ፫፻፴፰

**CONTENTS**

**The Addis Ababa City Government Regulation Defining Procedures and Organization of the Kenema Pharmacy……………page** 338

**ደንብ ቁጥር ፴፩/፪ሺ፪**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎችን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣ**

የአዲስ አበባ ከተማ ከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ የህክምና መገልገያዎች እና መድሃኒቶችን ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በሽያጭ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርብ ማ□ረ□ በማስ□ለ□፤

ይህም ለህዝቡ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል የሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ ስለታመነበት እና የድርጅቱን አሠራርና አደረጃጀት በህግ መደንገግ በማስ □ለ□፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ የከተማው ማዕከል የክፍለ የከተማና የቀበሌ አስፈፃሚና የማዘጋጃቤት አገል□ሎት አካላት እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፩ አንቀጽ ፸፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፤

**Regulation No. 31/2010**

**The Addis Ababa City Government Cabinet Regulation Defining Practice and Organization of the Kenema Pharmacy**

**WHEREAS** it is necessary to make the Addis Ababa city Kenma pharmacy enterprise provide quality and effective medical supply and pharmaceuticals to the Addis Ababa cities residents at affordable price ;

**WHEREAS** it is be lived that this contributes a very grave role to upgrade the health service delivery, to the public and it is necessary to define by the law the practice and origination of the enterprise;

**NOW, THEREFORE,** the Addis Ababa city Government cabinet pursuant to article 79 of the Addis Ababa city Government center sub city and kebele executives and Municipal service organs re establishment proclamation No. 15/2009 has issued these regulation;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

**??? ???**

**? ??? ?????? ?**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከነማ ፋርማሲዎች ድርጅትን አደረጃትና አሠራር ለመደ ንገግ የወጣ ደንብ ቁጥር ፴፩/፪ሺ፪» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **«አስተዳደር»** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፪. **«ከነማ ፋርማሲዎች ድርጅት»** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሙሉ ባለቤት ነት የከነማ ፋርማሲዎች እና ከነማ መድሃ ኒት መደብሮችን በማዕከል እንዲያስተዳድር በአዋጅ ቁጥር ፲፭/፪ሺ፪ መሰረት የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፡፡

፫. **«ከነማ ፋርማሲዎች»** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ ክፍለ ከተሞች“ ቀበሌዎች መድኃኒቶችን እና የህክምና መገ ልገያዎችን በችርቻሮ ለህዝብ በማከ ፋፈል ተግባር ላይ የተሰማሩ በፋርማሲስት የሚ መሩ የከነማ መድኃኒት ቤቶች ነው፡፡

፬. **«ከነማ መድሃኒት መደብሮች»** ማለት በአስ ተዳደር በተለያዩ ክፍለ ከተሞች መድሃኒ ቶችን እና የህክምና መገልገያዎችን በችር ቻሮ ለህዝብ በማከፋፈል ተግባር ላይ የተሰ ማሩ በድራጊስት የሚመሩ መድሃኒት ቤቶች ናቸው::

፭.**«ቢሮ»** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳ ደር ጤና ቢሮ ነው፡፡

፮. **«ጠቅላላ ንብረት»** ማለት የድርጅቱ የማይን ቀሳቀስናተንቀሣቃሽ ንብረቶች፣ ድርጅቱ ገና ያልተቀበላቸው ገቢዎች፣ ጥሬ ገንዘብና የባ ንክ ሂሣብ ሲሆን ግዙፍ ያልሆኑ ንብረቶ ችን በቅድሚያ የተከፈሉ ወጪዎችንና ለሎ ችገቢ መሆንያለባቸውሂሣቦችንይጨምራል፡፡

፯.**«ካፒታል»** ማለት ድርጅቱ በተቋቋመ ጊዜና ከዚያም በኋላ መንግሥት የሚመድብለት የተ ጣራ ጠቅላላ ንብረት ነው፡፡

## PART ONE

## General Provision

**1. Short Title**

This regulation may be cited as "the Addis Ababa City Cabinet Regulation defining the practice and organization of the Addis Ababa city kenema pharmacy enterprise regulation number 31/2010".

**2. Definition**

In this regulation:

1. "**Government**" means The Addis Ababa City Government.
2. "**Kenema pharmacies enterprise**" means pharmacy's enterprise means a public enterprise fully owned by the city government.
2. "**Kenema pharmacies**" means A public enterprise established per Art (56) of the proclamation 15/2009 fully owned by the city government, to administer the kenema pharmacy and pharmaceutical station.
4. "**Kenma pharmaceutical station**" means established in different sub cities to retail pharmaceutical and medical supply and administered by dragist
5. "**Bureau**" means the Addis Ababa City Government health "bureau.
6. "**Total assets**" mean the fixed and current assets, receivables, cash and bank balance of an enterprise, including intangible assets, deferent charges, and other receivables.
7. "**Capital**" means the value of the total assets that a given enterprises secures as per these regulations and as at any time of the assignment of net total asset to it by the government.

፰. **«ኦዲተር»** ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲(፪) በተመለከተው መሠረት ማናቸውንም የድርጅቱን ሂሣብ የሚመረምር የተፈጥሮ ሰው ወይም የህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፱. **«የተጣራ ትርፍ»** ማለት ድርጅቱ በበጀት ዓመቱ ከመድሃኒት ሽያጭ እና ከሌሎች ክፍያዎች ከተገ ኘው ገቢ ላይ ለሥራ ማስኬጃ፣ ደመወዝ ባግባቡ ወጪ የተደረጉ ድምር ሂሣቦች እና የዕርጅና ቅናሽ ወለድና ልዩ ልዩ ክሶች ተቀንሰው የሚቀረው ሂሣብ ነው፡፡

## ፫. ?? ? ?? ?? ???

ደንቡ በአዲስ አበባ ከተማ ከነማ ፋርማሲዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፬. ተጠሪነት

፩. የድርጅቱ ተጠሪነት ለአዲስ አበባ ከተማ ሥራ አስኪ ያጅ ይሆናል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌም ቢኖርም ቢሮው በውክልና ድርጅቱን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

## ፭. የድርጅቱ ችሎታ

ድርጅቱ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል በስሙ ይከሣል፣ ይከሰሳል፡፡

## ፮. ?? ??? ???? ???

፩. ጠቅላላ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፳፰ ሚሊየን ፩፻፸፪ ሺ፫፻፵፩.፷፯ (ሃያ ስምንት ሚሊዬን አንድ መቶ ሰባ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ብር "ከስልሣ ሰባት ሣንቲም)፤

፪. በዓይነት የተከፈለ ብር ፲፮ሚሊየን ፫፻፶፫ሺ ፯፻፲፰.፲፬(አስራ ስድስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃምሣ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ አስራ ስምንት ብር ከአስራ አራት ሣንቲም)፤

፫. በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ብር ፲፩ሚሊየን, ፰፻፲፰ሺ, ፮፻፸፫.፶፫ (አስራ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከሃምሣ ሶስት ሣንቲም)፡፡

## ፯. ?? ? ??? ??

የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ በማዕ ከል ሆኖ እንደተገልጋዩ ህዝብ ብዛት በተለያዩ ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች ፋርማሲዎች" መድሃኒት መደብ ሮች ይኖሩታል፡፡

8. **"Auditor"** means a natural person or a body given by law legal personality to credit the account of an enterprise as per the provisions of sub article 2 of article 10 of these Regulations.

9. "**Net profit**" means the remaining balance that exists after expenditures , operational costs and salaries property disbursed in the fiscal Year , depreciation interest and various taxes have been deducted from revenues and other payments

## 3. Scope of Application

This regulation shall be applicable to the Addis Ababa City government Kenema pharmacy.

## 4. Accountability of the Enterprise

1. Accountability of the enterprise shall be to the city manager.
2. Notwithstanding to sub article 1 of this article, the bureau supervise the enterprise by delegation.

## 5. Legal Capacity of the Enterprise

The enterprise shall owned property conclude contract; sue and be sued.

## 6. The Capital of the Enterprise

1. Total authorized capital; birr 28, 172, 391. 67 (twenty eight million one hundred seventy two thousand three hundred forty one sixty seven cents;
2. Payment in kind of the part of the capital birr 16, 353, 718. 14 (sixteen million three hundred fifty seven thousand seven hundred eighteen and fourteen cents;
3. Money paid in cash birr 16,818,673.53 (eleven million eight hundred eighteen thousands six hundred seventy three and fifty three cents.

## 7. Head Office of the Enterprise

The head office of the enterprise shall be at the city center and may have pharmacy's and pharmaceticular station at sub cities and kebeles according to the number of customers.

**፰. <u>አደረጃጀት</u>**

ድርጅቱ:-

፩.የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪.ዋና ስራ አስኪያጅ፣ እና ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ፤

፫.ለሥራው አስፈላጊ የሆኑሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፱. <u>□□ር□ቱ ኃላፊነት</u>**

□□ር□ቱ እዳዎች ሊሽፈኑ የሚችሉት ባለው ጠቅላላ ንብረት ብቻ ነው፡፡

**፲. <u>ዓላማዎች</u>**

ድርጅቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩. ለአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ጤና መሠረታዊና አስፈላጊ የሆኑ ጥራቸውና ፈዋሽነቸው የተረጋገጡ የህክምና መገልገያዎችና መድሃኒቶችን በዓይነትና በመጠን በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ፤

፪. መሠረታዊ አስፈላጊ መድሃኒቶችና የህክምና መገልገያዎች ዋጋእንዳይንር የገበያ መረጋጋት መፍጠር፤

፫. በህበረተሰቡ ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለሚያደርሱ ስር ሰደድ ህመሞች እና በአጣዳፊ ወረርሽኝ የሚከ ሰቱ በሽታዎችንለመከላከልናለመ□□ስየሚያስችሉ መሠረታዊ መድሃኒቶችን ለህበረተሰቡ ማቅረብ፤

፬. በቦር□ በሚወሰነው መሠረት ከመድሃኒትና ከህክምና መገልገያዎች ሽያጭ የሚያገኘ□ን የተጣራ ትርፍ የጤና አግልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ማዋል፤

፭.ተ□ ማሪ የከነማ ፋርማሲዎችንና መድሃኒት መ□ብሮ ችን መክፈት፡፡

**<u>??? ???</u>**

**<u>□ቢሮ□ና □ቦር□ ስል□ንና ተ□ባራት</u>**

**፲፩. <u>የቢሮው ሥልጣንና ተግባር</u>**

ቢሮ□ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩ የውጭ ኦዲተሮችን ይሰይማል፡፡

**8. <u>Organization</u>**

The enterprise shall have:

1. A management board;
2. A general manager deputy general managers as may be necessary and;
3. The necessary staff.

**9. <u>Liability of the Enterprise</u>**

The enterprise may not be kind held liable beyond its total assets.

**10. <u>Objectivities</u>**

The enterprise shall have the following objective to:

1. Provide to the Addis Ababa city people essential medicine and safety medical supply in quantity and kind at reasonable price;
2. Create Market stabilization by controlling price inflation of essential medicine and medical supply;
3. Provide the public essential medicine caple of preventing and healing chronic and epidemic diseases, which affect the society's health at large;
4. Utilize net profit author the sale of the pharmaceutical and medical supply according to the decision of the board;
5. Open up additional kenma pharmacies and pharmaceutical stations.

## <u>PART TWO</u>

## <u>Power and Function of the Bureau and The Board</u>

**11. <u>Power and Function of the Bureau</u>**

The bureau shall have the following power and function to:

1. Appoint External auditors;

፩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ ለቢሮ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ድርጅቱን በበላይነት ይመራል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ:-

ሀ. የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፣ ደመወዝና አበል ይወስናል፣ ያሰናብታል፤

ለ. ለድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ቅጥርና ምደባ ስንብት፣ ደመወዝና አበል ያጸድቃል፤

ሐ.የድርጅቱን የሥራ (ዕቅድ) በጀትና የአሠራር መመሪያ ያጸድቃል አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፤

መ.የድርጅቱን የረጅም ጊዜ ብድሮች እና ክሬዲቶችን ያጸድቃል፤

ሠ. በድርጅቱ ህልውና ላይ ወሳኝነት ያላቸውን ቋሚ ንብረቶች ሽያጭ ያጸድቃል፤

ረ. የድርጅቱ ሂሣቦችና ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

ሰ. ድርጅቱ ከመድሃኒት ወይም የህክምና መገልገያዎችሽያጭየሚያገኘውንየትርፍ መጠን ይወስናል፤

ሸ. የዓመትና የየሩብ ዓመት ሪፖርት ለቢሮው እና ለሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡

## ፲፬. <u>የቦርዱ ስብሰባና ተጠያቂነት</u>

፩ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይሰበስባል፤

፪. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ አባላት ሲጠይቁ በማናቸውም ጊዜ ሰብሳቢው የቦርዱን ስብሰባ ይጠራል፤

፫. ከቦርዱ አባላት መካከል አብላጫው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

፬. ቦርዱ በሰብሰባው ላይ በተገኙት በድምጽ ብልጫ ይወስናል፣ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል ከሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፭. □ቦር□ ውሣኔ ህግን በሚጥስበት ጊዜ በውሣኔው □ተሳተ□ እያንዳንዱ የቦርድ አባል በሚከተለው ሀላፊነት በግልም ሆነ በጋራ ተጠያቂ ይሆናል፣ ሆኖም በሀሣብ የተለየ የቦርድ አባል ለሚከተለው ሀላፊነት አይጠየቅም፤

፮. ቦርዱ ከድርጅቱ ሠራተኞች መካከል መርጦ ፀሐፊ ይመድባል፡፡ሆኖም ፀሐፊው ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም::



1. The board shall administer the enterprise with enterprise without prejudice to the power and function of the bureau set out under Art (11) of this regulation;
2. Without prejudice to the General provision provided for in sub (1) of these Art, the Board shall:
   a. Appoint and dismiss the General Manager of the enterprise and fix his salary and allowance.
   b. Approve the employment, assignment and dismissal of those officers of the Enterprise accountable to the general Manager, including their salaries and allowance.
   c. Approve the internal regulations of the enterprise as well as its work programmer and budget
   d. Approve long term loans and credits of the enterprise;
   e. Approve the sale of fixed assets that may not affect the existence of the enterprise;
   f. Ensure that proper books of accounts are kept for the enterprise;
   g. Fix the amount of that the enterprise obtains as of the sale of modern medical supply;
   h. Submit annual and quarterly report to the bureau and to the City Manager.

## 14. <u>Liability and Meeting of the Board</u>

1. The board shall meet at least once in month;
2. The chairman shall call a meeting of the boa- rd at any time, in cases of urgency or where more than have of the board members so request;
3. There shall be a quorum where a majority of the members are present;
4. The board shall take decision by Majority vote in case of a tie; the chairman shall have a casting vote;
5. The board May assign non-voting secretary among the enterprise's employees;
6. The General Manager may participate on the meeting of the board without vote;

፯. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለ ድምጽ በቦርድ በሰብሳቢው ይሳተፋል፤

፰. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል::

## ፲፭. የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር

፩. ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል::

፪. ዋና ሥራአስኪያጅ:-

ሀ. የድርጅቱን ሥራ ያደራጃል ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ. ድርጅቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ለሚያደርጋቸው ግን ኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፤

ሐ. በሥሩ ለሚገኙት ክፍት ቦታዎች ለእሱ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችንና ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ተግባራቸውን ይከታተላል፤

መ. በድርጅቱ የውስጥ ደንብና አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሌሎች ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያሰናብታል ፣ደመወዛቸውንና አበላቸውን በቦርዱ ያስወ ስናል፤

ሠ. የድርጅቱን ሂሣቦች በአግባቡ እንዲያዝ ያስደርጋል የድርጅቱን የባንክ ሂሣብ ያንቀሳቅሳል፤

ረ. የድርጅቱን የሥራ ኘሮግራምና በጀት እንዲሁም የውስጥ ደንብ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

ሰ. የየሩብ ዓመቱ የሥራ ዕቅድና ሪፖርት ለቦርዱና ለቢሮ ያቀርባል፤

ሸ. በሥራው ሂደት ላይ የሚመክርና በሥራ ግምገማዎች በዕቅዶችና ውሣኔዎች ላይ የሚወያይ መማክርት ያቋቁማል፤

ቀ. በቦርድ የሚሰጡት ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል::

7. Where the board's decision, violets the law, each board member participating in the decision shall be held liable for the ensured Liability's; however, a board member decanting in the decision, may not be held liable;
8. The board may issue its meeting procedure with out prejudice to the provision in this art.

## 15. Power and Duties of the Enterprise's Manger

1. Accountability of the enterprise's General Manager shall be to the board.
2. The General Manager shall:
   a. Organize direct, administered control the enterprise;
   b. Represent the enterprise as regards its relationship with third parties;
   c. Subject to the approval of the board, employee assigns and dismisses the officers of the enterprise accountable to him and defines their function;
   d. Employ, assign and dismiss other employees of the enterprise in s accordance with the internal regulation of the enterprise and the appropriate law, and determined their salaries and allowance;
   e. Keep proper books of account of the enterprise and open and operate bank Accounts to the enterprise;
   f. Prepare and submit to the board the internal regulation as well as the work programmer and budget of the enterprise, and implement same up on approval;
   g. Submit quarterly plan and report to the board and the bureau;
   h. Establish process council delivarating on the plans discussion and decision of the process;
   i. Perform other duties assigned to him by the board.

## ??? ሶስት

## ል□ ል□ □ን□□ ች

### ፲፮. የድርጅቱ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት

፩. ድርጅቱ ትክክለኛና የተሟሉ የሂሣብ መዛግብት ይኖሩታል፤

፪. ድርጅቱ አግባብነት ባላቸው የንግድ ህጎች መሠረት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ይመራል፡፡

### ፲፯. የሂሣብ ዓመት፣ ሂሣብ መዝጋትና ዓመታዊ ሪፖርት

፩. የድርጅቱ የሂሣብ ዓመት ከ ሐምሌ ፩ እስከ ሰኔ ፴ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ይሆናል፤

፪. ድርጅቱ በዓመት አንድ ጊዜ ሂሣቡን ይዘጋ ጿል ዓመታዊው ሂሣብ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ መዘጋት አለበት፤

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የድርጅቱን ሂሣብ በወቅቱ አለመዝጋት በኃላፊነት የሚያስጠይቅ ይሆናል፡፡

### ፲፰. ስለ ግብር ወይም ቀረጥ ክፍያ

፩. የግብር ወይም ቀረጥ ክፍያን በሚመለከት አግ ባብ ያላቸው ሕጎች በድርጅቱ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፪.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፲ ቢኖርም ድር ጅቱ በሌላ ሕግ መሠረት ከግብር ወይም ቀረጥ ከዳኝነት አገልግሎት ነጻ ለመሆን ያለውን መብት ይህ ደንብ አያስቀርበትም፡፡

### ፲፱. ሂሣብ የማስመርመር ግዴታ

የድርጅቱን ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ፣ ለሂሣቡ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሣቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## PART THREE

## Miscellaneous provision

### 16. Enterprise accounting principles

1. The enterprise shall have accurate and complete books of account;
2. The enterprise shall be Guide by the relevant commercial laws accounting principle.

### 17. Finical year closing of accounts and annual report

1. Finical year of the enterprise shall be from June 1 to July 30 In E.C;
2. The enterprise shall close its account at least once in a year; the annual closing of accounts shall be completed within three months following the end of the financial Year;
3. Failure to close, in due time, the accounts of an enterprise in accordance with sub-article 2 of this Article may entail liability.

### 18. Payment of Taxes and duties

1. The relevant laws concerning taxes and duties shall be applicable to enterprise.
2. Nothing in this regulation shall affect the right of the enterprise to be exempted from taxes and duties and any other right under any other law.

### 19. Obligation to cooperate

Any person who has received paid or expanded or is in of the accounts of, the money or property of the enterprise shall, when requested, have the obligation to produce to auditors the accounts and furnish the necessary information.

## ፳. <u>የማውጣት ስልጣን</u>

ቦርዱ ይህንን ደንብ ለማስፈጠም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፳፩. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

፩. የፍትሐብሄር ህግ፣ የንግድ ህግ እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፲፬ እንደአግባቡ በዚህ ደንብ ላይ ተፈፃሚዎች ይሆናሉ፤

፪. ማንኛውም ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፳፪. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በአዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**መጋቢት ፱ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## 20. <u>Power to Issue Directive</u>

The board may issue directive to assists the implementation of this regulation.

## 21. <u>Applicable law</u>

1. Civil code ,the code and public enterprise establishment proclamation 25/1992 shall be applicable to this regulation where appropriate;
2. Any regulation or practice in consistence this regulation shall not be applicable with matters covered under this regulation.

## 22. <u>Effective Date</u>

This regulation shall come in to force at the date of its publication on Addis Negari Gazeta.

**Done at Addis Ababa**

**On this 18th Day of March, 2010**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa**